የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፳፩ ቀን ፪ሺ፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 10
ADDIS ABABA 30th December, 2010

ማውጫ

CONTENTS

አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፰/፪ሺ፫ ዓ.ም

ለመሠረታዊ አገልግሎቶች አሰጣጥ ድጋፍ ምዕራፍ ሁለት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ለማግኘት ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ......ገጽ ፭ሺ፮፻፺፩

Proclamation No. 698/2010

African Development Fund Additional Loan Agreement for the Basic Services Program Phase II Project Ratification Proclamation.... Page 5691

አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፰/፪ሺ፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለመሠረታዊ አገልግሎቶች አሰጣጥ ድጋፍ ምዕራፍ ሁለት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ፸፪ሚሊዮን፮፻ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት /ሰባ ሁለት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት/ ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ዲሴምበር ፲፭ ቀን ፪ሺ፲ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሣሥ ፲፪ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለመሠረታዊ አገልግሎቶች አሰጣጥ ድጋፍ ምዕራፍ ሁለት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ለማግኘት ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፰/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

PROCLAMATION No. 698/2010.

A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

WHEREAS a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan in the amount of 72,600,000 U.A (seventy two million six hundred thousand Units of Account) for additionally financing Basic Services Program Phase II was signed in Addis Ababa on the 15th day of December, 2010;

WHEREAS the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the Financing Agreement at its session held on the 21st day of December 2010;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "African Development Fund Additional Loan Agreement for the Basic Services Program Phase II Project Ratification Proclamation No. 698/2010".

ያንዱ ዋጋ 2.30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ዲሴምበር ፲፭ ቀን ፪ሺ፲ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 2100150023294 በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፸፪ሚሊዮን፮፻ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት /ሰባ ሁለት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሣሥ ፳፩ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2. <u>**Ratification of the Agreement**</u>

The Loan Agreement No.2100150023294 signed in Addis Ababa on the 15th day of December 2010 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund is hereby ratified.

3. <u>**Power of the Ministry of Finance and Economic Development**</u>

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 72,600,000 U.A (seventy two million six hundred thousand Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. <u>**Effective Date**</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 30th day of December, 2010

GIRMA WOLDEGIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት